**ለመስከረም 20/21 ጉባኤ የአጀንዳና የውሳኔ ነጥቦች አስተዋፅኦ** (2005)

## *አጀንዳ ነጥብ አንድ*
## *ስለምርጫውና የማጣራቱ ሂደት መክሸፍ ስለ ህዝባችን ድል መከበር ጉዳይ*

የግንቦት 97 ምርጫም ሆነ የተከተለው የውጤት ማጣራት ሂደት በኢህአዴግና በምርጫ ቦርዱ ፀረ ህዝብ መመሳጠር በጭብርብር አክትመው የኢህአዴግ የሸፍጥ አሸናፊነት ታውጅዋል። እኛም ህዝባችንም ይህንን ውጤት አልተቀበልነውም። አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ምርጫው ተጭበርብሩዋል፤ ሂደቱ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ካሳየው ጉጉት አልመጠነም፤ ነፃ ምርጫን አስመልክቶ በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን መስፈርቶች በሚያሟላ ሁኔታ አልተካሄደም የሚል ግልፅ ድምዳሜ ላይ ደርሷል። በመሆኑም ህዝባችን በዚህ የምርጫ ሂደት ታግሎና ተሰውቶ የተጎናፀፈውን ድል ለማስመለስ ሰላማዊና ህጋዊ ትግሉ ሳያሰልስ መቀጠል ይኖርበታል። ይቀጥላል።

ይህንን ስንል እኛ የኢትዮ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ከህዝባችን ጎን ቆመን የምናካሂደው ትግል በግንቦት 97 ምርጫ ህዝቡ ያገኘው የድምፅ ድል ይከበር የሚል ትግል ብቻ አይደለም። ከዚህ አልፎ በዚህ ምርጫ ሂደት ሳቢያ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የተጎናፀፋቸውን ሌሎች ከምርጫ ሰሞን አልፈው የሚሄዱ መሰረታዊ ድሎችንም ለማስከበር የሚደረግ ታሪካዊ ተጋድሎ እንደሆነ ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል።

ተደጋግሞ እንደተባለው ሰላም፤ ለውጥና ዴሞክራሲ በሚሉ እሴቶች ዙሪያ በሃያኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮ ህዝብና ታጋይ ልጆቹ ሲያካሂዱት የቆዩት የትግል ታሪክ እነዚህን የተያያዙ እሴቶች ከማስተጋገዝ ይልቅ እርስ በርስ እያጣፉ የተካሄዱበት ታሪክ ነው። ለውጥ ስንሻ በሰላም ስም በሩ ሲዘጋብን፤ ሰላም ስንሻ በለውጥ ስም በሚካሄድ አመፅ ሃገራችን ስትታመስ ሰላምም፤ በጎ ለውጥም፤ ዴሞክራሲም ተነፍገን በአስከፊ አዙሪት ውስጥ ስንኳትን ዘመናት አስቆጥረናል።

የግንቦት 97 የምርጫ ሂደት መሰረታዊ ድልና ለመጭው ትውልድ ሲታወስ የሚኖርበት ዋና ምክንያት የሰላማዊ ለውጥ፤ የዴሞክራሲና የብሄራዊ እርቅ እሴቶች በግንባር ቀደምነት ከተሰለፉ ሃይሎች አልፈው በጠቅላላ በህብረተሰቡ እንደሰረፁ የታየበትና ህዝባችን ለዘመናት ተቆላልፎ የቆየበትን አጥፊ አዙሪት ሰባብሮ አዲስ ታሪካዊ ምእራፍ የፈነጠቀበት ሂደት መሆኑ ነው።

የግንቦት 97 የምርጫ ሂደት በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝባችን በሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ተማምኖ መንግስት በአመፅ ሳይሆን በድምፅና በሰላማዊ ዘዴ ሊለወጥ ይችላል ብሎ ተንቀሳቅሶና ተሰውቶ በሰላማዊ ዘዴ መንግስት የቀየረበት ሂደት ነው።

የግንቦት 97 የም-ርጫ ሂደት ህዝባችን ይህንን ድሉን ለማስከበር አሁንም ለምንም አይነት የፀረ ህዝቦች ትንኮሳ ሳይመቻች የኢህአዴግ መሪዎች ሊቀሙት ያሰቡትን የመስዋእትነት ፍሬ የሆነውን ድሉን አሁንም በሰላማዊ ትግል ለማስከበር እየተንቀሳቀሰ ያለበት ሂደት ነው።

የግንቦት 97 የም-ርጫ ሂደት አሁንም በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝባችን በእርቀ ሰላም እሴት በማመን አስከፊውን የአሸናፊና ተሸናፊ አዙሪት በመስበር ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በህዝብ ድምፅ ለተሸነፈው ኢህአዴግ ያቀረቡትን የብሄራዊ አንድነት የሽግግር መንግስት ጥሪ ተቀብሎ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝበት ሂደት ነው።

የህዝባችን ድል ይከበር ብለን ስንንቀሳቀስ ህዝባችን የተጎናፀፋቸውን እነዚህን ሁሉ ታሪካዊ ድሎች የጥቂቶችን የስልጣን ጥም ለማርካት ብቻ አሳልፈን ሰጥተን አክ እንትፍ ብለን ወደተፋነው የአፈናና የአመፅ ስርአትና አዙሪት አንመለስም ማለታችን እንደሆነ ማንም ሊገነዘበው ይገባል። ከዚህም በመነሳት እነዚህን ድሎች እያስተጋገዝን የምንራመድበት አዲስ የትግል ምእራፍ በምንያያዝበት በአሁኑ ወቅት ስለቀጣዩ ትግል ያለንን አማራጭ ከማቅረባችን በፊት በኢህአዴግ አሸናፊነት ተጠናቀቀ ስለተባለው የምርጫ ሂደት ያለንን አቋም እንደሚከተለው በግልፅ

እናስቀምጣለን

1.ኛ ምርጫ ቦርዱ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 104/1/ በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተፅእኖ ነፃ የሆነ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል የሚለውን ድንጋጌ በመፃረር በወገናዊነትና ካለው ገዥ ፓርቲ ጎን ቆሞ የምርጫውን ሂደት ከዳር እስከዳር የበከለው መሆኑን በመገንዘብ፤

2. የምርጫ ህጉን አዋጅ አንቀፅ 23 እና አንቀፅ 24 ስለ ታዛቢዎች የተወዳዳሪዎች ተወካዮች የሚደነግጉትን በመተላለፍ ኢህአዴግ በሸፍጥ አሸነፈባቸው ከተባሉት 327 የምርጫ ወረዳዎች በድምሩ በ.......ቱ የተወዳዳሪዎች ተወካዮች ተባርረው፤ ተደብድበውና ታስረው ቆጠራው የተወዳዳሪ ፓርቲ ተወካዮች ባልተገኙበት የተካሄደ መሆኑን በማጤን

3. ሌሎች ከባድ ግድፈቶችና ህገወጥ አሰራሮች በዚህ መልክ ቢዘረዘሩ..........

4. የምርጫውን ውጤት የማጣራቱ ሂደት በኢህአዴግና በምርጫ ቦርዱ ከስምምነት ውጭ በተወሰዱ እርምጃዎች የተኮላሸ መሆኑን በማመን

5. በአጠቃላይ የምርጫው ሂደት የኢትዮጵያን ህዝብ አመኔታ ባላገኘበትና በአለም አቀፍ ደረጃም በእርግጥ ገለልተኛ የሆኑ ታዛቢዎች ይህ ምርጫ በአንድ በኩል የኢት ህዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ጉጉት በማይመጥን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በነፃ ምርጫ ጉዳይ በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን መስፈርቶች ባላሙዋላ ሁኔታ የተካሄደ መሆኑን ማጋለጣቸውን ~~በመመዝገብ~~

ሀ) የኢት ህዝብ የምርጫውን ውጤት እንዳልተቀበለው ሁሉ እኛ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሲቪክ ማህበራት ተጠሪዎችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በግንቦት 97 ምርጫ ውጤት ተብሎ የኢህአዴግ አሸናፊነት መታወጁን ህጋዊነት ላለማወቅ ወስነናል

ለ) ከዚህ ከዳር እስከዳር በተጭበረበረና በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ፊት እውቅና ባላገኘ የምርጫ ውጤት የሚቋቋመው ፓርላሜንትም የሃገሪቱ ህገ መንግስት በአንቀፅ 54/1/ *''የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሁሉን አቀፍ፤ ነፃ፤ ቀጥተኛና ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርአት በየአምስት አመቱ በህዝብ ይመረጣሉ''* ተብሎ የተደነገገውን ከዳር- እስከዳርና በገፍ በመጣስ የሃገሪቱን ህገ መን-ግስት ተፃርሮ የተሰየመ መሆኑን አምነንበታል

ሐ) ከዚህ ከፅንሱ ፀረ ህገ መንግስት በሆነ መልክ የተሰየመ ፓርላማ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 56 እና አንቀፅ 73 መሰረት ተጠቅሞ የፌዴራል መንግስቱን የህግ አስፈፃሚ አካል የማደራጀትም ሆነ በምክር ቤቱ ውስጥ አብዛኛውን መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች ከምክር ቤቱ አባላት መሃከል ይመርጣል የሚሉትን አንቀፆች በተግባር ለማዋል የሞራልም ሆነ ህጋዊ ብቃት ስለሌለው በዚህ ምክ-ር ቤት የተሰየመ መንግስትም ህገ መንግስቱን በተፃረረ መልክ የሚቋቋም መንግስት መሆኑን በይፋ እናስታውቃለን።

## *አጀንዳ ቁጥር ሁለት*
## *ሃገሪቱ ካለችበት የምርጫ ማግስት ቀውስ መውጫ ስትራቴጂያችንን በሚመለከት*

የተያያዝነው ትግል ህዝባችን በመስዋእትነት ባስመዘገባቸው የሰላማዊ ለውጥና የብሄራዊ እርቅ ድሎች ላይ ለመገንባት እንጂ እነሱን ለመናድ የሚካሄድ ባለመሆኑ ሃገራችን ካለችበት የም-ርጫ ማግ-ስት ቀውስ እንድትወጣ የሚካሄደው ትግል ሁለት መሰረታዊና በምንም አይነት የማይነጣጠሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ወይም አላማዎች ይኖሩታል።

አንደኛው ህዝባችን ሞቶ ተሰውቶ በግንቦቱ ምርጫ ያስገኘውና ዛሬ በገዥው ፓርቲና በዚህ ድርጅት ቁጥጥር ስር ባለው የምርጫ ቦርድ በጠራራ ፀሃይ የተዘረፈው ድምፁ የሚከበርበትን ሁኔታ የማመቻቸት ተጋድሎ ነው። ይህ እኛ የኢት ዴሞክራሮችና አገር ወዳድ ሃይሎች እስከ መጨረሻው የምንዋደቅለት ህዝባዊ አላማ በመሆኑ የትግላችን አንድ መሰረታዊ ይዘት "የህዝብ ድምፅ ይከበር" የሚለው ሆኖ ይቀጥላል። ሃገራችን ካለችበት ቀውስ ትወጣ ዘንድ ይህ የማይታለፍ የመፍትሄ ሃሳብ የሚሆነው የኢህአዴግ መሪዎች ለማስመሰል እንደሚሞክሩት "የጥቂቶችን የስልጣን ጥም ለማርካት" አይደለም። የህዝብ ድምፅ ካልተከበረና የተሰረቀ ድምፅ በፀረ ህዝብ አመፅ ታግዞ ለመን-ግስት ስልጣን የሚያበቃበት አሰራር ከቀጠለ በግንቦቱ የምርጫ ሂደት አሸናፊ ሆኖ የወጡት "ስልጣን በህዝብ ምርጫ" "ስልጣን በሰላማዊ ሂደት" የሚሉት ወርቃዊ እሴቶች በህዝባችን ፊት ተአማኒነት የሚያጡበትና ተመልሰው የሚከስሙበት አደጋ አለ። የህዝብ ድምፅ ይከበር የሚል መፈክር አንግቦ የሚካሄደው ትግላችን በዚህ ሰፊና ዴሞክራሲያዊ ራእይ የሚመራና ሃገራችንን ከዚህ አደጋ ለመጠበቅ የሚካሄድ ትግል እንደሆነ ለኢህአዴግ መሪዎችም ሆነ ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

ሁለተኛ የግንቦት 97 ምርጫ ሂደት ሳቢያ አሸናፊ ሆነው ከወጡት እሴቶች ሌላው የብሄራዊ እርቅ ሃሳብ እንደሆነ ግልፅ ነው። የህዝቡን ድምፅ ለማስከበር የምናደርገው ትግል ይህንን አዲስ እሴት ለማጎልበትም እንጂ በዚህ እሴት ኪሳራ የምናካሂደው ትግል አይሆንም። በመሆኑም አንዱ ወገን አሸናፊ ሌላው ወገን ተሸናፊ ሆነው ከሚቀላለፉበት አዙሪት ወጥተን ዴሞክራሲ፤ ህብረተሰባችንና አገራችን በሙሉ አሸናፊ ሆነው ለሚወጡበት የብሄራዊ አንድነት ሽግግር መንግስት ጥሪያችንን አንግበን በህዝብ ድምፅ ለተሸነፈው ኢህአዴግ የብሄራዊ እርቅ እጃችንን መዘርጋቱን እንቀጥልበታለን። ከነዚህ አላማዎች በመነሳት እኛ የኢትዮ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች፤

1ኛ. ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የቀውስ መውጫ ዴሞክራሲያዊና ገንቢ ሃሳቦች የጠቅላላው የህብረተሰባችን ጥያቄዎች መሆናቸውን በመገንዘብ

2ኛ. እነዚህ ሃሳቦች በተግባር እንዲውሉ የኢህአዴግን መሪዎችን ብቻ ሳይሆን የዚህን ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች የሚያካትት ሰፊ ብሄራዊ ውይይት አስፈላጊ መሆኑን በማጤን

3ኛ. የህዝብ ድምፅ በተከበረበት ሁኔታ ኢህአዴግንም የሚያካትት የብሄራዊ አንድነት የሽግግር መንግስት መመስረት በሃገራችን የተጀመረውን ሰላማዊ የዴሞክራታይዜሽን ሂደት የሚያጎለብት ፍቱን መፍትሄ መሆኑን በማመን

ሀ) የህዝቡ ድምፅ እንዲከበር የምርጫው ሂደትና ውጤት ሁሉም ወገኖች በሚስማሙበት ገለልተኛ አካል ግልፅነት ባለው ሁኔታ ተመርምሮ በህዝባችን ፊት ተአማኒነት የሚያገኝ የኢትዮጵያ ህዝብ በሰላማዊ ምርጫ ሂደት ያለውን እምነት በሚያጎለብት መልክ ፍትሃዊ እልባት የሚያገኝበት መንገድ ለማመቻቸት ኢህአዴግ በአስቸኳይ ከህብረተሰቡ ተወካዮች ጋር ድርድር እንዲከፍት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፤

ለ) በህዝብ ድምፅ የተሸነፉት የኢህአዴግ መሪዎች ህብረተሰቡ የዘረጋላቸውን የእርቅና የሰላም ጥሪ ተቀብለው የበሄራዊ አንድነት የሽ-ግግር መን-ግስት ስለሚቋቋምበት ዘዴ ባስቸኳይ ድርድር እንዲጀምሩ እንጠይቃለን

ሐ) የኢትዮ ህዝብ፤ የሃገሪቱ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች የሲቪክ ማህበረሰቡ አባላት፤ ወጣቶች፤ ሴቶች፤ ተማሪዎች፤ ሰራተኞች፤ ገበሬዎች ነጋዴዎችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይህንን ጥሪ በመደገፍ ከዳር እስከዳር እንደ አን-ድ ሰው ሆነው ለትግል እንዲነሱ አገራዊ ጥሪ እናቀርባለን

መ) የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች በአንድ በኩል ይህንን ሃገራዊ ጥሪ በመደገፍ መሪዎቻቸው አወንታዊ መልስ እንዲሰጡ ግፊት ማድረግ ህዝባዊ፤ አገራዊና ዴሞክራሲያዊ ግዴታቸው መሆኑን ተገን-ዝበው ይህንን ግፊት እንዲያደርጉና በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የዜግነት ግዴታቸውን ለመወጣት በያሉበት በጥሞና ከህብረተሰቡ ጋር በሃገር ጉዳይ መወያየት እንዲጀምሩ ጥሪ እናስተላልፋለን

## አጀንዳ ነጥብ ሶስት
## በጭብርብሩ ከተገፉና የመፍትሄ ሃሳቦች ተቀባይነት ካላገኙ ስለሚካሄደው ትግል

የኢህአዴግ መሪዎች ይህ የቀውስ መውጫና በህዝባዊ ድል ላይ ሌሎች ህዝባዊ ድሎች ለመገንባት የተደረገ ጥሪ አላአግባብ ትርጉም ሊሰጡትና በአሻፈረኝ ባይነት ሊቀጥሉ ይችላሉ። አልፈው ተርፈው ይህንን አገራዊ ጥሪ የሌለውን የአመፅና የህገወጥነት ገፅታ በመስጠት ራሳቸው በህዝባችን ላይ ለማዝነብ ለሚያሴሩት አመፅ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንደሚሞክሩ በይፋ እያየናቸው ነው። በመሆኑም የዚህን ዴሞክራሲያዊና ገንቢ የመፍትሄ ሃሳብ ምንነትም ሆነ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ስለም-ንጠቀምበት የትግል ስልት ለነዚህ ጥቂቶችም ሆነ ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲ በግልፅ ማሳየት ያስፈልጋል።

አንደኛ ይህ ትግል መላ ህብረተሰባችን ለሰላምና ለዴሞክራሲ የሚያካሂደው ትግል ነው። በመሆኑም የኢህአዴግን መሪዎች በም-ርጫ ማጭበርበራቸውና አገኘን በሚሉት የሸፍጥ ውጤት ገፍተውና ይህንን የብሄራዊ እርቅ ሃሳብ አሻፈረን ማለት ከቀጠሉ ከእንግዲህ መብታችንንና ድላችንን ለማስከበር የምናካሂደው ትግል እስካሁን ለፀረ ህዝቦች አመፅ ሲያመቻቸን በቆየው ተራ በተራ እየተነሱ ተራ በተራ የመታፈን ስትራቴጂ አይመራም። ከእንግዲህ እንዳለፉት ዘመናት አንዴ ተማሪው፤ አንዴ ገበሬው፤ አንዴ መምህሩ አንዴ ደግሞ ታክሲ ነጂው፤ አንዴ የዝህ ፋብሪካ ሰራተኛ ሌላ ጊዜ ደግሞ በተራው የዚያኛው ፋብሪካ ሰራተኛ፤ አንዴ በዚህ ክልል ሌላ ጊዜ ደግሞ በዚያኛው፤ አንዴ በዚህ ተቃዋሚ ድርጅት ሌላ ጊዜ ደግሞ በሌላ ተቃዋሚ ድርጅት ....የሚለው ስልት አክ-ትሞ የህብረተሰባችን የተለያዩ ክፍሎች በአንድ ወቅት እንደ አንድ ሰው ተነስተው የሚያካሂዱት ተጋድሎ መሆን እንዳለበትና እንደሚሆንም በግልፅ ማስቀመጥ እንወዳለን።

ሁለተኛ ትግሉ ሰላማዊ፤ ህጋዊና በህገ መንግስቱ ማእቀፍ ውስጥ የሚደረግ የመብትና የአገር ጉዳይ ተጋድሎ ነው። አመፅ የሚያስፈልጋቸው ጥቂት ቀቢፀ ተስፋዎች ብቻ ናቸው። መብቴንና አገሬን ብሎ በአንድነትና በሚልዮን እየተቆጠረ የሚንቀሳቀስ ሃያል ህዝብ በምንም መልኩ፤ ከሩቅም ከቅርብም አመፅ የሚያስፈልገው የትግል ስልት አይኖረውም። ዛሬ ከነዚሁ ጥቂቶች በስተቀር ይህንን ሁኔታ የማይገነዘብ ማንም ያለ አይመስለንም። በመሆኑም አመፀኞቹን በህዝብ ላይ ለሚጠነስሱት የአመፅ ሴራ ምንም ሰበብ በማይሰጥ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ የህዝብ ትግል ማእበል፤ ህገ ወጦቹን ፍፁም ህጋዊ በሆነ ዘዴ፤ ህዝብ ለህዝብ ለማናከስ በብሄር ጥላቻ ፕሮፓጋንዳ የተሰማሩትን ሃይማኖትና ብሄር ሳንል በአንድ በተባበረና በሚተጋገዝ የኢትዮጵያውያን ጠንካራ ክንድ ልንቋቋማቸው መነሳታችንን ከወዲሁ ግልፅ ማድረግ እንወዳለን።

ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው እውነታዎች በመነሳት እኛ የኢትዮ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች

1ኛ. ሃገራችንን ከገባችበት ቀውስ ለማውጣት የኢህአዴግን መሪዎች ወደ ድርድር ለማምጣት የሚደረገው ትግል ፍፁም ሰላማዊ፤ ህጋዊና ባለው ህገ መንግስት መአቀፍ ውስጥ የሚካሄድ ትግል መሆኑን በማረጋገጥ

2ኛ. ይህ በህገ መንግስቱ ማእቀፍ ው-ስጥ የሚገኝ የትግል ስልታችን "ማንም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት" እንዳለው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 30 የተደነገገውን የሰላማዊ ሰልፍ መብት፤ እንዲሁም በዚሁ ህገ መንግስት በአንቀፅ 42/1/ሀ የተደነገገውን የስራ ማቆም መብትና በሌሎች ህጋዊ ስልቶች እየተጠቀመ መካሄድ የሚችል መሆኑን በማረጋገጥ

3ኛ. ትግሉ ለኢህአዴግ የፀረ ህዝብ አመፅ ሰበብ እንዳይሰጥና ሰላማዊ ህኖ እንዲቀጥል ታጋይ ህዝባችን በተለመደው ብስለቱ በከፍተኛ ዲሲፕሊን ታጅቦ መካሄዱ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው በማመን

4ኛ. በዚሁ መልክ ደግሞ በዴሞክራቶችና በሃገር ወዳዶች ሰፈር በምንም ምክንያት ይሁን በምን ሊንፀባረቅ የሚችል የልዩነትና የመከፋፈል ፍንጭ ለኢህአዴግ የአመፅ ሴራ የልብ ልብ ሰጥቶ ለአስከፊ ሁኔታዎች በሩን የሚከፍት አሉታዊ አካሄድ መሆኑን በጥሞና በማጤን

ሀ) የኢህአዴግ መሪዎች በጉባኤያችን የተደረገላቸውን የብሄራዊ ድርድር ሃሳብ አሻፈረኝ በማለት በህገ ወጥና ህገ መንግስቱን በተፃረሩ አካሄዶች የተሰየመው ፓርላማ መስከረም 30 ቀን የሚከፈት ከሆን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 42/1/ሀ በሚፈቅደው መሰረት ከሰኞ መስከረም ሰላሳ ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ለአርባ ስምንት ሰአት በመላ ሃገሪቱ በሁሉም የስራ መስኮች የሚፀና ጠቅላላ ስራ ማቆም እንዲካሄድ የወሰንን ስለሆነ የኢትዮ ህዝብ ለዚህ ትግል ራሱን ካሁኑ ማዘጋጀት እንዲጀምር ጥሪ እናስተላልፍለታለን

ለ) የኢህአዴግ መሪዎች ማንኛውንም የዴሞክራሲና የእርቅ ሃሳብ አሻፈረን ብለው ህዝባችን ደግሞ በበኩሉ ድምፁንና ድሉን ለማስከበር ከባድ መስዋእትነት እንዲከፍል እየጋበዙበት ባለበት ሁኔታ በዚህ ህገ ወጥ ፓርላማ ገብቶ እታገላለሁ ማለት ትግሉን የሚከፋፍልና ብሎም በህዝባችን ላይ የኢህአዴግ መሪዎች በማውጠንጠን ላይ ላሉት አመፅ የልብ ልብ የሚሰጥ አደገኛ አካሄድ በመሆኑ የኢህአዴግ መሪዎች በህዝብ ትግል ለድርድር እስኪቀርቡ ድረስ የየድርጅቶቻችን ተመራጮች ከዚህ እርምጃ እንዲቆጠቡ ጥሪ እናደርግላቸዋለን

ሐ) ለሃገራችን ችግሮች ሰላማዊና ገንቢ ሃሳቦች ይዘን የምናደርገው ተጋድሎ ፍፁም ሰላማዊና ህጋዊ ሆኖ መቀጠል ስለሚገባው በሰላማዊ ሰልፎች፤ በስራ ማቆምና በሌሎች ህጋዊ የትግል ስልቶች በምንሰማራበት ወቅት ዋና መሳሪያዎቻችን አንድነትና ዲሲፕሊን በመሆናቸው ከመሃላችን ሰርገው በመግባት ማን-ኛውንም ህገ ወጥ ተግባር በመቀስቀስ ሁከት ለማንሳትና ለኢህአዴግ መሪዎች የአመፅ ሰበብ ለመስጠት የሚሰሩ ግለሰቦችን ህዝቡ በስነ ስርአት ለፀጥታ ሃይሎች እንዲያስረክብና እነዚህ ሃይሎች ደግሞ እነዚህን ወንጀለኞች እየያዙ በስነ ስርአት ህግ ፊት ከማቅረብ አልፈው በሰላማዊው ህዝብ ላይ ምንም አይነት ህገ ወጥ ርምጃ እንዳይወስዱ አገራዊ ጥሪ እናስተላልፍላቸዋለን

መ) መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ.ም. በሃገራችን በበርካታ ከተሞችና በአለም ዙሪያም እንደዚሁ በያለበት በሚደረጉ ሰልፎች አማካኝነት የቀረበውን የብሄራዊ ውይይት ጥሪ አሻፈረን ካሉ በኋላ ይህንኑ ብሄራዊ ጥሪ ለማጠናከር ከመስከረም 30 ጀምሮ በስራ ማቆም አማካኝነት የሚደረገውን ጥሪ የኢህአዴግ መሪዎች በህገ ወጥና በአመፅ ለማደናቀፍ የሚንቀሳቀሱና በአሻፈረን ባይነታቸው የሚፀኑ ከሆነ ቀጣዩን ትግል በሚመለከት ህዝቡ በማንኛውም ትንኮሳ ሳይሸነፍ ስለቀጣዩ ትግል የሚሰጠውን መመሪያ በጥሞናና በጨዋነት በተጠንቀቅ እንዲጠብቅ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።